
# የተወጣለት የትረካ ችሎታ እና የቋንቋ አጠቃቀም በደራሲት እታለም እሸቴ የረጅም ልብወለድ መጻሕፍት፡ በ"ምንዳ" እና በ"ህልመኛዋ እናት"

አጭር አስተያየት ከዓለሙ ተበጀ

በ2001 ዓ. ም. "ምንዳ" የሚለውን የመጀመሪያ ባለ 556 ገጽ የረጅም ልብወለድ መጽሐፏን አሳተመች። አሁን በቅርቡ በ2004 ዓ. ም. ደግሞ ሁለተኛ መጽሐፏን "ህልመኛዋ እናት"ን በ473 ገጽ አቅርባልናለች፤ ደራሲት እታለም እሸቴ። የብዙ ሴት ጸሐፍትን የአጫጭር ልብወለድ እና የግጥም ሥራዎች ታትመው አንብቤያለሁ። በሀገራችን ሴቶች የተጻፉ ወጥ (ኦሪጂናል) የረጅም ልብወለድ መጻሕፍት ግን ብዙ ያሉ አይመስለኝም:: ያውም ከአንድ አልፈው ሁለት፣ በገፃቸውም ብዛት የዳጉሱ ሥራዎች ያቀረቡልን ሴት ፀሐፍት አላጋጠሙኝም። እናም እታለም 'በኢትዮጵያ የረጅም ልብወለድ የሴት ፀሐፍት መድረክ አዲስ እየወጣች ያለች ፋና ወጊ ብዕረኛ' ትመስለኛለች። ለዚህም ይመስለኛል የጉምቱውን ጸሐፊና ሀያሲ የአቶ አስፋው ዳምጤን አድናቆትና እደጊ ተመንደጊ ሙያዊ ምርቃት ያገኘችው፣ ቀልባቸውን የሳበችው ። ለ"ምንዳ" በጋዜጣ ላይ የግምገማ ጸሑፍ ለንባብ አብቅተዋል፣ ለ"ህልመኛዋ እናት" በሀገር ፍቅር ቴአትር በተካሄደ ምርቃት ላይ በክብር እንግድነት ተገኝተዋል።







ሁለቱም መጽሐፍት በየራሳቸው ገፀ-ባህርያት ግለ-ታሪኮች ላይ የሚጓዙ ቢሆንም፤ በጭብጣቸው (በመልዕክታቸው) ሀገር አቀፍ ቁምነገር ባላቸው ችግሮች ላይ ያተኩሩ ናቸው። "ምንዳ" በኤዲስ ሕሙማን፣ በደም ብቀላና ተዛምደው ባሉ ማህበራዊና ባህላዊ ችግሮች፤ "ህልመኛዋ እናት" ደግሞ በትዳር ላይ በሚከሰተው የፆታ ጭቆና ላይ።

በሁለቱም መጻሕፍት የገፀ-ባህርያቱ የቋንቋ አጠቃቀም ተፈጥሯዊ ነው። በዚህም ታሪካቸው በደራሲዋ የፈጠራ ጥበብ ኅብር ፈጥሮ አንድ ወጥነትን እያገኘ በአንድ ትልቅ ቦይ ሳይደናቀፍ ይፈሳል። ባለታሪኮቹ በንግግራቸው እራሳቸውን ሆነው ነው የሚዘልቁት። ሕይወታቸውም፣ በጠቅላላ ሰብዕናቸው ከሀገራችን የተቀዳ ነው። በብዙ መጻሕፍት ላይ የሚታየው፤ ባለታሪኮቹ

እራሳቸውን ሆነው ከመዝለቅ ይልቅ፣ የየጸሐፍቱ አፍ ሆነው፣ የራሳቸው ያልሆነ አጓጉል ፍልስፍና፣ አመለካከት ወዘተ ተሸካሚ/ተናጋሪ የመሆን ዕጣ ፈንታ አላጋጠማቸውም። በሌላ አገላለፅ ፀሐፊዋ በታሪኩ ዓለም አንድ ጊዜ ካመጣቻቸው (ከተወለዱ) በኋላ የራሷን የቋንቋ አጠቃቀም፣ የአነጋገር ዘይቤ፣ ሀሳብ ወዘተ በግድ አልጫነቻባቸውም። በነፃነት እራሳቸውን ሆነው በታሪኩ ውስጥ ይኖራሉ። እንደማንም ሰው፣ በዕለት ተዕለት ሕይወታቸው የሚጠቀሙበትን የየራሳቸውን ተራ ቋንቋ ሲጠቀሙ እናገኛቸዋለን። የየራሳቸውን የአነጋገር ባህሪም እንደያዙ ታሪካቸውን ጀምረው ይጨርሳሉ።

በሁለቱም መጻሕፍት እታለም የመረጠችው የአተረካክ ስልት አንደኛ መደብ ነው። በየመጻሕፍቷ ውስጥ ካሉት ባለሪኮች ውስጥ ተራኪ ባለታሪክ መርጣልን እየተረኩልን እንጓዛለን።

በ“ምንዳ” ውስጥ ዋናው ባለታሪክ ከልጅነቱ ጀምሮ እስከ ጎልማሳነቱ በሚዘልቅ የዕድሜ መንገድ ርቀት፣ ዙሪያው ካሉ ሰዎች ጋር የተቀናጀ ታሪኩን ያወጋናል። ይህ የአተራረክ ስልት፣ ተራኪው ባለታሪክ ባለበት የጊዜና የቦታ ውሱንነት ምክንያት (እሱ በማይኖርበት ቦታና ጊዜ ወይም በሆዳቸው የሚያስቡትን፣ የሚናገሩትንና የሚያደርጉትን ስለማያውቅ) በመጽሀፉ ውስጥ ያሉ የሌሎች ሰዎችን ታሪክ ለመተረክ ሊያስቸግረው ይችላል። ያውም ለአዲስ ጸሐፊ። እታለም በዚህ በኩል ምንም ችግር አላየሁባትም። እንደውም የዚህን ውሱንነት፣ ለልብ ሰቀላ (አንባቢያኗን እያጓጓች) ለማስኬድ ውጤት (ኢፌክት) ተጠቅማበታለች። ምንም እንኳ አንድ ሰው ተራኪ ሆኖ እስከመጨረሻቸው ቢዘልቅም፣ እሱ በሌለበት ቦታና ጊዜ ሌሎች ተቃናጅ ባለታሪኮች የሚከውኑትንና የሚያስቡትን ከሌሎች ሶስተኛ ሰዎች እየሰማ፣ እሱም እኛም እየጠረጠርን፣ የታሪኩን መዳረሻ ለማወቅ በጉጉት እንጓዛለን። በአንድ ቀጥ ብሎ በሚፈስ የታሪክ ሂደትም እየተጓዝን፣ ሳናውቀው ልባችን እንደቆመ፣ የግጭቱ ጡዘት (ክላይማክስ) ከልቀቱ ደርሶ ከሚደመደምበት ኬላ እንደርሳለን።

በ“ህልመኛዋ እናት”ም የተጠቀመችው የአንደኛ መደብ ትረካ ስልትን ቢሆንም በብዙ ጉዳዮች ለየት ይላል። እነኝህም የእታለም የትረካ ችሎታና ብቃት የተፈተነባቸው፣ ይህንንም በሚገባ ያለፈችባቸው ይመስሉኛል። በ”ምንዳ” ትረካ የጊዜ እለፍ ተቀደሙ አፈሳሰስ ቀጥ ያለ ነው። እንደዚህ ሆነ፣ ከዚያም እንደዚህ ሆነ፣ ቀጥሎም … በሚል ዓይነት አካሄድ። “ሕልመኛዋ እናት” ግን ያለፈና የአሁን ጊዜ ክስተቶች በሚገባ እየተጣመሩ፣ ሶስት ገፀ-ባህርያት በቅብብሎሽ ዓይነት ተራኪነት የሚያወጉን ከጊዜና ከቦታ አንፃር ውስብስብ ታሪክ ነው። መጽሐፉ የሚጀምረው በዋናዋ ባለታሪክ ታሪክ የጊዜ መስመር ሲለካ ወደመጨረሻ ላይ ካለው አንጓ ነው። ግና ወደኋላ በመሄድ በምልሰት (ፍላሽባክ)፣ ከአሁን ጋር እያጣመረ፣ ከታዳጊነቷ እስከ እናትነቷ ድረስ ያለውን የረጅም ጊዜ ታሪኳን ይነግረናል። ኡጋንዳ፣ ለንደን፣ አዲስ አበባ፣ ናዝሬት፣ ሻሸመኔ፣ አሜሪካ እያሽከረከረ። ይህንን ታሪኳን ዋናዋ ባለታሪክ የምታወጋን በቀጥታ አይደለም። እየተጠቀሰች ነው። ሌሎች ሁለት አስተኔ ገፀ-ባህርያት (በአንድ ክፍል ውስጥ የዩኒቨርስቲ ትምህርታቸውን አብረው የሚከታተሉ አንዲት ኡጋንዳዊትና ሌላ ኢትዮጵያዊ ወጣት፣ እሷ ከዋናዋ ባለታሪክ ጋር ደባል የመኖሪያ ቤት ተከራይ፣ እሱ ደግሞ ኢትዮጵያዊ በመሆናቸው ሰበብ) ከራሳቸው የጋራ ሕይወት ጋር በተቀናጀ ሁኔታ ዋናዋ ባለታሪክ የፃፈችውን ግለ-ታሪክ እየተቀባበሉ በማንበብ ነው የሚተርኩልን። እንደ “ህልመኛዋ እናት” ባብዛኛው በቅብብሎሽ (ከአንድ ተራኪ በላይ በሆኑ ባለታሪኮች) በምልሰት በሚነገር ታሪክ ላይ የተመሰረተ ረጅም ልብወለድ መጻፍ በሀገራችን ደራሲዎች የተለመደ አይደለም። የቅብብሎሹን ነገር በዓሉ ግርማ ብቻ በ”ኦሮማይ” ላይ መጠቀሙን አስታውሳለሁ። እናም እታለም ይህን በሀገራችን ያልተለመደ የአፃፃፍ ስልት መከተሏ - ያውም ገና አዲስ ፀሐፊ ሆና - እና አንድ ጊዜ ማንበብ

ጀምረው ካልጨረሱት በስተቀር እያጓጓ ልብ የሚሰቅል "ህልመኛዋ እናት"ን ማቅረቧ የሚያስደንቅ ነው።

ቀደም ሲል እንደገለጽኩት አንደኛ መደብ ትረካ ካለበት አስቸጋሪነት በተጨማሪ፡

- ባብዛኛው የአለፈ ታሪክ በምልሰት የሚነገርበት፣
- ከተፈፀሙበት ጊዜና ቦታ አንፃር የተለያዩ የታሪክ አንጓዎች በአንድ ላይ እየተቀናበሩ የሚፈሱበት፣ በመጋቢነትም ኅብር ፈጥረው የአንድ ዋና ታሪክ አካል የሚሆኑበት፣

እንደመሆኑ "ህልመኛዋ እናት" የእታለም የትረካ ችሎታ የተፈተነበት ነው ማለት ይቻላል። በቅድሚያ የምልሰት ትረካን መጠቀሟ ድንቅ ምርጫ ነው። ይህ በምልሰት የምትነግረን ታሪክ እንዳያሰለቸን፣ መጽሐፉን የጀመረችበት የታሪክ ኬላ ከሚያጓጓ ቦታ ላይ መሆኑ ትልቅ ብልጠት ነው። ከዚያም ወደኋላም ወደፊትም እየሄደች፣ የአሁንና የአለፈ ጊዜ ክስተቶችን አሳምሮ በማቀናበር፣ ሕይወት ያለው ቦይ ፈጥረው ያለእንከን እንዲፈሱ በማስቻል ደግሞ ትልቅ ችሎታዋን አስመስክራለች። አሁን በመከወን ላይ ያለው የመጽሐፉ ታሪክ ሳይቆም፣ የትላንቱም ታሪክ የአሁን አካል በመሆን ስምሙነት ፈጥረው፣ አንድም ሁለትም እየሆኑ፣ ሙሉውን አንድ ትልቅ ታሪክ ይሰጡናል።

"ህልመኛዋ እናት" ውስጥ የምናገኛት ዋናዋ ባለታሪክ ትርሲት ሰብዕና፣ የእናት ፍቅር ተምሳሌት ነው። ለዚህም ይመስለኛል መፅሓፉን ገዝተው ታሪኳን ካነበቡት ወዳጆቼ ውስጥ፣ አንደኛው "የእኛ እናቶች እንዴት ያሳዝናሉ! ወንድነቴን ጠላሁት!" በማለት እንደገለፀው፣ የሀገራችን አብዛኛዎቹን ሴቶች ሕይወትና ይህም ሕይወት የተዋቀረበትን ወግ እንዲንጠይቅ የማድረግ ሃይል ያላት። በጠቅላላ እታለም በሁለቱም የረጅም ልብወለድ መጻሕፍት - በ"ምንዳ" እና በ"ህልመኛዋ እናት" - በኢትዮጵያ እና/ወይም በስደት ዓለም የኢትዮጵያዊያንን የዕለት ተዕለት ሕይወት አቅርባለች። በተዋጣለት የአተራረክ ችሎታዋ፣ የባለታሪኮቹ የራሳቸው በሆነ የቋንቋ አጠቃቀሟም የሕይወታቸው ሀዘን፣ ደስታ፣ ክፋት፣ በጎ ሥራ ወዘተ ስሜታችንን ሰርስሮ እንዲሰማን አድርጋለች።